## <u>መመሪያ ቁጥር 1116/2018</u>

## <u>የህዝብ በዓላት አከባበር መመሪያ</u>

የሕዝብ በዓላት ኃይማኖታዊ፣ ባህላዊ እና ታሪካዊ ሥርዓታቸውን ጠብቀው በሰላም፣ በድምቀት እና የዜጎችን የእርስ በእርስ መልካም ግንኙነትና መተሳሰብ በሚያጎለብት ሁኔታ እንዲከበሩ ለማድረግ የበዓላቱን የአከባበር ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የህዝብ በዓላት ለሀገር እና ለህዝብ ሊያበረክቱ የሚችሉትን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አስተዋጽኦ ማበርከት እንዲችሉ የሚመለከታቸው እና ባለድርሻ አካላት በቅንጅትና ትብብር የሚሰሩበትን አግባብ በዝርዝር መደንገግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የህዝብ በአላት ለሀገራችን የገጽታ ግንባታ እና የዘላቂ ባህል ጥበቃ የሚኖራቸውን አዎንታዊ ሚና በአግባቡ መጠቀም በማስፈለጉ፤

የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 1334/2016 አንቀጽ 18(2) መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

   ይህ መመሪያ "**የህዝብ በዓላት አከባበር መመሪያ ቁጥር** 1116/2018" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **<u>ትርጓሜ</u>**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ፡-

1) “**አዋጅ**” ማለት የህዝብ በዓላትን እና የበዓላትን አከባበር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 1334/2016 ነው፤

2) “**ሚኒስቴር** ወይም **ሚኒስትር**” ማለት እንደቅደም ተከተላቸው የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

3) “**የፀጥታ አካል**” ማለት የፌዴራል ወይም የክልል ፖሊስ፣ መከላከያ፣ ደህንነት፣ ሚሊሻ፣ ደንብ አስከባሪ ወይም ማንኛውም የህዝብን ሰላምና ደህንነት ለማስጠበቅ በመንግስት የተደራጀ አካል ነው፤

4) **"ሚዲያ ወይም የመገናኛ ብዙሃን"** ማለት በመንግስት ወይም በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 መሰረት ተቋቁሞ መረጃ ለህዝብ የሚተላለፍበት ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ መጽሔት፣ ጋዜጣ ወይም ማንኛውም መረጃ በድምጽ፣ በምስል ወይም በጽሁፍ የሚተላለፍበት የመገናኛ ዘዴ ነው፤

5) በአዋጁ አንቀጽ 2 ስር የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያም ተፈፃሚ ይሆናሉ።

## ክፍል ሁለት

## የህዝብ በዓላት አከባበር

### ንዑስ ክፍል አንድ

### የዘመን መለወጫ በዓል አከባበር

3. የዘመን መለወጫ በዓል ቅድመ-ዝግጅት

ሚኒስቴሩ፡-

1) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የዘመን መለወጫ በዓል አንድ ወር ሲቀረው ስለበዓሉ ታሪካዊና ባህላዊ ይዘቶች፣ በዓሉ ለሀገርና ህዝብ ስለሚኖረው ፋይዳ እና ተያያዥ ጉዳዮች የተለያዩ አስተማሪ ፕሮግራሞችን በመቅረጽ በመገናኛ ብዙሀን፣ በምክክር መድረኮች፣ ወይም በሌሎች አማራጮች ለህዝብ እንዲደርሱ ያደርጋል።

2) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የዘመን መለወጫ በዓል ባህላዊና ታሪካዊ ይዘቱን በጠበቀ አግባብ ለሀገርና ለህዝብ ዘላቂ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንዲውል ተገቢውን ያደርጋል።

3) ሀገራዊ የባህልና የጥበባት ፌስቲቫል ያዘጋጃል፣ ለህዝብ ክፍት ያደርጋል።

4) እስከ ዘመን መለወጫ በዓል ያሉ ቀናትን የህዝብ አብሮነትን በሚያሳድጉ፣ ብሩህ ተስፋን በሚያጭሩ እና የስራ መነሳሳትን በሚፈጥሩ ቃላት ወይም ሃረጋት ይሰይማል፣ የሚመለከታቸውን ያስተባብራል።

5) የወቅቱ መገለጫ የሆነውን አደይ አበባ በሀገራዊ ተምሳሌትነት እንዲተዋወቅና እንዲለማ ያደርጋል።

4. ዘመን መለወጫ በዓላት ዋዜማ የሚከናወኑ ተግባራት

1) የሀገሪቱ ፕሬዚዳንት ወይም ጠቅላይ ሚኒስትር በበዓሉ ዋዜማ የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት እና ከበዓሉ አከባበር ጋር ተያይዞ ታሳቢ ሊደረጉ ስለሚገባቸው ጉዳዮች በመንግስት የመገናኛ ብዙሃን ለመላ የሀገሪቱ ሕዝብ መልዕክት ያስተላልፋል።

2) የክልል ፕሬዚዳንቶች ወይም ምክትል ፕሬዚዳንቶች እና የከተማ መስተዳድር ከንቲባዎች በክልሎች ወይም ከተማ መስተዳድሮች በሚወጡ ህጎችና በሚዘረጉ ስርዓቶች መሰረት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት ለህዝብ ሊያስተላልፉ ይችላሉ።

3) የሐይማኖት መሪዎች በበዓሉ ዋዜማ የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት እና ከበዓሉ አከባበር ጋር ተያይዞ ታሳቢ ሊደረጉ ስለሚገባቸው ኃይማኖታዊ ጉዳዮች የህዝብ የመገናኛ ብዙሃንን በመጠቀም ለሕዝቡ መልዕክት ያስተላልፋሉ።

4) በዚህ አንቀፅ የተጠቀሱት እንደተጠበቁ ሆነው ሚኒስቴሩ ፡-

ሀ/ በበዓሉ ዋዜማ ብሔራዊ የችቦ ማብራት ስነ-ስርዓት ያከናውናል፣ በመርሀ-ግብሩ የሀገር መሪዎችና ዲፕሎማቶች እንዲገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል።

ለ/ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ዘመን አቆጣጠርን ያስተዋውቃል፣ መርሀ-ግብሮችን በመቅረጽ እውቀቱ እንዲተላለፍ ያደርጋል።

ሐ/ የህዝብ ለህዝብ የመልካም ምኞት ስጦታ መስጫ መርሃ-ግብር እንዲከናወን ያደርጋል፣ የሚመለከታቸውን ያስተባብራል።

5. <u>በዘመን መለወጫ በዓል ዕለት የሚከናወኑ ተግባራት</u>

ሚኒስቴሩ፡-

1) ከመገናኛ ብዙሀን ጋር በመተባበር ስለበዓሉ አስተማሪ እና አዝናኝ ባህላዊና ኪነ ጥበባዊ መርሀ- ግብሮች እንዲተላለፉ ያደርጋል።

2) የዘመን መለወጫ በዓል በሰላም እንዲከበር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል።

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## የአድዋ ድል በዓል አከባበር

6. <u>በአድዋ ድል በዓል የሚከናወኑ ተግባራት</u>

ሚኒስቴሩ፡-

1) የድል በዓሉ ለቀጠናዊና አህጉራዊ ትስስር የድርሻውን በሚያበረክትበት አግባብ የማስተዋወቅና የማልማት ተግባር ያከናውናል::

2) በዓሉን በተመለከተ ክልሎች በዜጎች መካከል ተግባቦትንና ብሄራዊ አንድነትን በሚያጠናክርበት አግባብ እንዲያከብሩ ያስተባብራል፣ ድጋፍ ይሰጣል::
3) በአድዋ ድል ዙሪያ ደረጃቸውን የጠበቁ የኪነ-ጥበብ ስራዎች እንዲስፋፉ ያበረታታል፣ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል::
4) የድል በዓሉን በተመለከተ የጥናትና ምርምር ስራዎችን ያካሂዳል::

## ንዑስ ክፍል ሦስት

## የአርበኞች የድል ቀን በዓል አከባበር

### 7. <u>የአርበኞች የድል ቀን በዓል ቅድመ ሁኔታ ተግባራት</u>

ሚኒስቴሩ ከጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ጋር በመተባበር፡-

1) የአርበኞች ድል በዓል ለሀገርና ህዝብ የሚኖረውን ፋይዳ አስመልክቶ የተለያዩ አስተማሪ ፕሮግራሞችን በመቅረጽ በመገናኛ ብዙሀን፣ በምክክር መድረኮች ወይም በሌሎች አማራጮች ለህዝብ እንዲደርስ ያደርጋል።

2) በበዓሉ ዕለት የሚከናወኑ መርሃ-ግብሮችን ያቅዳል፣ በመርሃ-ግብሮቹ የሚሳተፉ አካላትን በመለየት የስራ ድርሻ ያሳውቃል፣ ለፕሮግራሞቹ ውጤታማነት የሚያግዙ አስፈላጊ ዝግጅቶች መደረጋቸውን ይከታተላል፣ ይደግፋል።

3) በበዓሉ ዕለት ለሚደረጉ የማስታወሻ እና ሌሎች ክንዋኔዎች የሚያስፈልጉ የአበባ ጉንጉን እና ሌሎች ቁሳቁሶች እንዲዘጋጁ ያደርጋል።

4) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት በዓሉ ባህላዊና ታሪካዊ ይዘቱን በጠበቀ እና ለሀገርና ህዝብ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥቅምን በሚያስገኝ አግባብ እንዲከበር ያደርጋል።

### 8. <u>በአርበኞች የድል ቀን በዓል ዕለት የሚከናወኑ ተግባራት</u>

1) ሚኒስትሩና የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ፕሬዚዳንት ለሀገሪቱ ህዝቦች የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት ያስተላልፋሉ።

2) ሚኒስቴሩ ከጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ጋር በጋራ በመተባበር፡-

ሀ) በዓሉ የኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የመንግስት ተወካዮች፣ ወጣቶች እና ሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎችን ባካተተ መልኩ በማርሽ ባንድ ታጅቦ አራት ኪሎ በሚገኘው የአርበኞች የድል ሃውልት አደባባይ እንዲከበር ያደረጋል።

ለ) በበዓሉ ላይ የኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ገድል፣ ትውልድ ከድሉ ሊማር ስለሚገባው እና ሌሎች አስተማሪ ፕሮግራሞች እና መልዕክቶች እንዲተላለፉ ያደረጋል።

ሐ) ከመገናኛ ብዙሀን ጋር በመተባበር ስለበዓሉ አስተማሪ የሆኑ ፕሮግራሞች እንዲተላለፉ ያደርጋል፤ የበዓሉ አከባበር የሚዲያ ሽፋን እንዲሰጠው ያደርጋል።

3) ሚኒስትሩ እና የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ፕሬዝዳንት በአርበኞች የድል ሃውልት ስር ለመታሰቢያ የሚሆን የአበባ ጉንጉን፣ የሻማ ማብራት ሥነ-ሥርዓትና የህሊና ፀሎት እንዲደረግ ይሰራል።

4) ሚኒስቴሩ በዓሉ በሰላምና በድምቀት እንዲከበር ከፀጥታ እና ሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል።

5) ሚኒስቴሩ በዓሉ በመላ ሀገሪቱ ተከብሮ እንዲውል ከሚመለከታቸው የክልል እና የከተማ መስተዳድር አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል።

## ንዑስ ክፍል አራት

## የሰማዕታት ቀን ታስቦ ስለሚውልበት ሁኔታ

### 9. <u>በሰማዕታት ቀን ዕለት የሚከናወኑ ተግባራት</u>

1) ሚኒስቴሩ በዓሉ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር፣ የሀገር-ሽማግሌዎች፣ የመንግስት ተወካዮች፣ ወጣቶች እና ሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎችን ባካተተ መልኩ በማርሽ ባንድ ታጅቦ ስድስት ኪሎ በሚገኘው የሰማዕታት ሃውልት አደባባይ ያከብራል።

2) የሀገሪቱ ፕሬዝዳንትና ሚኒስትሩ የመገናኛ ብዙሀንን በመጠቀም ለሀገሪቱ ህዝብ የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት ያስተላልፋሉ።

3) ሚኒስቴሩ በሚታሰበው የሰማዕታት ቀን የተፈፀሙ ድርጊቶች፣ የተደረጉ ተጋድሎዎች እንዲሁም ትውልድ ከድሉ ሊማር ስለሚገባው ጉዳይ እና ሌሎች አስተማሪ ፕሮግራሞች እና መልዕክቶች እንዲተላለፉ ያደርጋል።

4) ሚኒስቴሩ ከመገናኛ ብዙሀን ጋር በመተባበር ስለበዓሉ አስተማሪ የሆኑ ፕሮግራሞች እንዲተላለፉ ያደርጋል።

5) ሚኒስትሩ በሰማዕታት ሃውልት ስር ለመታሰቢያ የሚሆን የአበባ ጉንጉን ያስቀምጣል፣

የሻማ ማብራት ሥነ-ሥርዓት ያካሂዳል፣ የህሊና ፀሎት ያስፈጽማል።

6) ሚኒስቴሩ አጠቃላይ የመታሰቢያ በዓሉን አከባበር ያስተባብራል።

7) ሚኒስቴሩ የሚመለከታቸው አካላትን በማስተባበር ቀኑ በሀገር አቀፍ ደረጃ ታስቦ እንዲውል ያደርጋል።

## ክፍል ሦስት

## የህዝብ በዓላት ልማት እና ቅንጅታዊ አሰራር

**10. <u>በአለም ቅርስነት የተመዘገቡ በዓላት አከባበር</u>**

1) በወካይ የሰው ልጆች ቅርስነት የተመዘገቡ ህዝብ በዓላት የባህሉ ባለቤት በሆነው ክልል ወይም ህዝብ ይከበራል።
2) ሚኒስቴሩ በአለም ቅርስነት የተመዘገቡ በዓላትን አከባበር ይደግፋል፤ ለመርሃ ግብሩ የሚመለከታቸውን አካላት ያስተባብራል፤

**11. <u>የህዝብ በዓላት ልማት</u>**

1) ሚኒስቴሩ የህዝብ በዓላት በዘላቂነት ለምተው ለዜጎች ሁለንተናዊ ጥቅም የሚውሉበትን አግባብ ይዘረጋል፤ በበዓላት ደረጃቸውን የጠበቁ ባህላዊ ምርቶች እና አገልግሎቶች እንዲቀርቡ ያደርጋል።

2) ሚኒስቴሩ በህዝባዊ በዓላት ልማት የሚመለከታቸውን አካላትን ያስተባብራል።

**12. <u>የህዝባዊ በዓላት ተደራሽነት</u>**

1) ሚኒስቴሩ ክልሎች የህዝባቸውን በዓላት በዝርዝር በመለየት የክልሉን ህዝባዊ በዓላት መቁጠሪያ፣ (Regional Holidays Calendar) እንዲያዘጋጁ ይደግፋል።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሚኒስቴሩ ደረጃውን የጠበቀ ሀገራዊ የህዝባዊ በዓላት መቁጠሪያ ያዘጋጃል፣ ለሚመለከተው አካል ያሰራጫል።

**13. <u>ከፀጥታ አካላት ጋር የሚደረግ ቅንጅትና ትብብር</u>**

ሚኒስቴሩ የህዝብ በዓላቱ በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ መሰረት ታሪካዊና ባህላዊ ስርዓታቸውን ጠብቀው በሰላም እና በድምቀት እንዲከበሩ ከፀጥታ አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል።

14. **<u>ከክልልና ከተማ መስተዳድሮች ጋር የሚደረግ ቅንጅትና ትብብር</u>**

ሚኒስቴሩ የህዝብ በዓላቱ በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ መሰረት ታሪካዊና ባህላዊ ስርዓታቸውን ጠብቀው እንዲሁም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም በሚያስገኝ መልኩ በመላ ሀገሪቱ ተከብረው ወይም ታስበው እንዲውሉ ለማድረግ ከሚመለከታቸው የክልል እና የከተማ መስተዳድር አካላት ጋር በተቀናጀ መልኩ ይሰራል።

15. **<u>ከመገናኛ ብዙሀን ጋር የሚደረግ ቅንጅት</u>**

ሚኒስቴሩ የህዝብ በዓላትን አከባበር፣ በዓላቱ ለሀገርና ህዝብ የሚኖራቸውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ፣ ታሪካዊና ባህላዊ ይዘት እና ሌሎች ከህዝብ በዓላት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን አስመልክቶ ከመገናኛ ብዙሀን ጋር በመተባበር ለህዝብ ትክክለኛ መረጃ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ የሚሰራጭበትን አግባብ ያመቻቻል፤ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል።

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

16. **<u>ተፈፃሚነት የማይኖራቸው መመሪያዎችና አሰራሮች</u>**

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚጣረስ ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በተመለከተ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

17. **<u>መመሪያውን ስለማሻሻል</u>**

ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህንን መመሪያ ሊያሻሽለው ይችላል።

18. **<u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ድረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**ሸዊት ሻንካ**

**የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር**

**ሚኒስትር**